# የዱር እንስሳት

# አደን አጠቃቀም የተሻሻለ

# መመሪያ ቁጥር 852/2014

# የዱር እንስሳት አደን አጠቃቀም የተሻሻለ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 852/2014

የዱር እንስሳት ሃብት ባልተቀናጀና አግባብነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና ለአደጋ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ፤

የዱር እንስሳት አደን አጠቃቀም የዱር እንስሳቱን ህልውና አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ዘርፉ ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት አደን አጠቃቀም የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል የወጡትን የዱር እንስሳት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17 (2) በተደነገገው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ የተሻሻለው "የዱር እንስሳት አደን አጠቃቀም የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 852/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/199 ነው፤
2. **"ደንብ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፤
3. በአዋጁ እና በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
4. **"ስፖርታዊ አደን"** ማለት ለመዝናኛና ለውጤታቸው ሲባል የተለያዩ የዱር እንስሳትን በሕጋዊ መንገድ የማደን ተግባር ነው፡፡
5. **"ፈቃድ"** ማለት ለስፖርታዊ አደን ሥራ ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
6. **"ፍጆታዊ አጠቃቀም"** ማለት የዱር እንስሳትን ከመኖሪያ ቦታው በመውሰድ ወይም በስፖርታዊ አደን፣ በራንች ወይም ዕርባታ በማሳደግ ለውጤታቸው (ሥጋ፣ ቆዳ፣ ላባ፣ ቀንድ፣ ጥርስ) ሲባል በመግደል የመጠቀም ስልት ነው፡፡
7. **"ኢ-ፍጆታዊ አጠቃቀም"** ማለት የዱር እንስሳትን ከመኖሪያ ቦታቸው ሳይወሰዱና ሳይገደሉ የመጠቀም ስልት ሲሆን የዱር እንስሳት ማስጎብኘትን፣ ፊልምና ፎቶግራፍ ማንሳትን ያካትታል፡፡
8. **"የአደን ቦታ"** ማለት ከብሔራዊ ፓርኮች፣ ከዱር እንስሳት መጠለያዎችና ከዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎች ውጭ በሆኑ ቦታዎች የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችንና ክፍት የማደኛ ቦታዎችን የሚያጠቃልል ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፡፡
9. **"የዱር እንስሳት ቁጥጥር አደን ቀበሌ"** ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር የተደረገ ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፡፡
10. **"የዱር እንስሳት አደን ኮታ"** ማለት ከየዱር እንስሳቱ ዝርያ ለአንድ ቁጥጥር አደን ቀበሌ ወይም ክፍት የማደኛ ቦታ በዓመት እንዲታደን የተፈቀደው የዱር እንስሳት ብዛት ነው፡፡
11. **"የአደን የነፍስ ወከፍ ዋጋ"** ማለት ህጋዊ አዳኞች ፈቃድ አግኝተው ለሚያድኑት ለእያንዳንዱ የዱር እንስሳት የሚከፍሉት የእንስሳው የነፍስ ወከፍ ዋጋ ነው፡፡

12."**የዱር እንስሳት ውጤት**" ማለት የማንኛውም የዱር እንስሳ ናሙና ወይም የእንስሳው አካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ፀጉር፣ ላባ ወይም ጎፍላው ሲሆን፤ ከእነዚህ የተሠሩ ውጤቶችንና ከእንስሳው መኖሪያ አካባቢ የተገኙትን የወፍ ጎጆ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ልጣጭ፣ አበባ፣ ማርና የመሳሰሉትን ነው፤

13."**ማርጣ**" ማለት ከታደኑ የዱር እንስሳት የሚገኝ የዱር እንስሳት ውጤት ነው፡፡

14."**ንስር**" ማለት ሥጋ በል የሆነ የአሞራ ዝርያ በበርካታ የዓለም ሀገራት የሚገኝ፣ መካከለኛ መጠን ያለውና በሥልጠና የታገዘ አደን የሚያካሂድ ወፍ ነው፡፡

15."**ፋልከነሪ**" ማለት በንስር አሞራ አማካይነት የሚከናወን የአእዋፍ አደን ነው፡፡

16."**ሳይተስ**" ማለት ሕልውናቸው ለዕልቂት አደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳትና እፅዋት ዓለም አቀፍ ንግድ ስምምነት ነው፤

17."**ባለሀብት**" ማለት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን በውል በመውሰድ የሚያለማና የዱር እንስሳት አደን እንዲከናወን የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

18."**ባለሙያ አሳዳኝ**" ማለት የአሳዳኝነት የሙያ ማረጋገጫ ያለው ቱሪስትንም ሆነ የአገር ውስጥ አዳኝን በአደን ተግባር ላይ የሚረዳ የአደን ባለሙያ ማለት ነው፡፡

19."**ሚኒስቴር**" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤

20."**ባለስልጣን**" ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡

21."**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

22."**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡

23.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ፍጆታዊ አጠቃቀም በላቀ መልኩ እንዲስፋፋና ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ንዑስ ዘርፉ ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ፤

2. ፍጆታዊው የዱር እንስሳት አጠቃቀም የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረግ፤
3. የፍጆታዊ የዱር እንስሳት አጠቃቀም ዘለቄታዊነትን በሚመለከት ተገቢውን ክትትል ለማድረግና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤
4. የዱር እንስሳት የአጠቃቀም ሥራን ለማሳለጥ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ ክፍተቶችን ለመዝጋትና ወጥነት ያለውን አሰራር መዘርጋት፤

4. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ የዱር እንስሳት አደንና የማሳደን ሥራ በሚከናወንባቸው ቦታዎችና በሚያከናውን ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለቁጥጥር አደን ቀበሌዎች</u>

5. **<u>ስለአደን ቀበሌዎች ይዞታና አጠቃቀም</u>**

1. በደንቡ አንቀጽ 6(3) መሠረት ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመተባበር በዕቅድ ላይ ተመስርተው የዱር እንስሳት የሚገኙባቸውን ቦታዎች በማጥናት አዳዲስ የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ያቋቁማል፤ የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ዳር ድንበር በመለየትና ካርታ በመሥራት ለባለሀብቶች ያቀርባል፡፡
2. የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ከጨረታ ውጭ ለባለሃብቶች ሊሰጡ አይችሉም፣ ጨረታውም ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ መሆን አለበት፡፡
3. ባለሃብቶች አዳዲስ የአደን ቀበሌዎችን በጨረታ ሲወስዱ በአደን ቀበሌው ውስጥ የሚሠሩትን መሠረተ ልማትና የጥበቃ ቦታውን ሥርአተ-አያያዝ ዝርዝር የሥራ መርሃ ግብር ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. በቁጥጥር አደን ቀበሌነት የሚከለሉ ቦታዎች በሰው ሠራሽ ተጽእኖዎች ያልተጎዱ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚፈለጉ ሆነው ስፋታቸው ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር ማነስ የለባቸውም፡፡
5. የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ስፋት ከ500 /አምስት መቶ/ ስኩየር ኪሎ ሜትር መብለጥ የለባቸውም፡፡

6. የቆዳው ስፋት ልዩነት ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ  ኪሎ ሜትር በታች ከሆነ በአንድ ላይ ተጠቃሎ የቁጥጥር አደን ቀበሌ የሚሆን ሲሆን ለተጨማሪው ስኩየር ኪሎ ሜትር በኮንሴሽኑ ስሌት መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ያስከፍላል፡፡
7. የቆዳው ስፋት ልዩነት 100 /አንድ መቶ/ እና ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ  ኪሎ ሜትር በላይ ከሆነ ግን እንደ አዲስ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ተቋቁሞ ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት ለባለሀብት ይሰጣል፡፡
8. አሳዳኝ ድርጅቶች በዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመጠቀም በይዞታ ማረጋገጫ ወይም በኮንሴሽን በተረከቡት የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ የሚያከናውኑት የሥራ እንቅስቃሴና የጥበቃ ቦታውን ሥርአተ-አያያዝ በተመለከተ በየሁለት ዓመቱ አንድ ጊዜ በክልሉና በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ክትትልና ጥናት ይካሄዳል፤ ክትትልና ጥናቱን መሠረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፡፡
9. ማንኛውም ባለሀብት የያዘውን የቁጥጥር አደን ቀበሌ በአግባቡና በዘለቄታዊነት ባለመጠቀሙ ምክንያት የያዘው የቁጥጥር አደን ቀበሌ የሀብት መራቆት ወይም መመናመን በክልሉና በባለሥልጣኑ ክትትልና ጥናት ከተረጋገጠ ባለይዞታነቱ ይሰረዛል፤ ሌላ ቦታም መያዝ አይፈቀድለትም፡፡
10. የቁጥጥር አደን ቀበሌው የሚገኝበት ክልልና ባለሀብቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ለዳር ድንበር መለየት የሚያስፈልጉ ምልክቶችን ወይም ጉልቶችን በግልጽ ቦታ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡
11. በቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ዳር ድንበር መካከል የ3 (ሦስት) ኪ. ሜትር ደጀን ወይም ነፃ መሬት መኖር አለበት፡፡
12. የቁጥጥር አደን ቀበሌው በሚገኝበት አቅራቢያ የሚገኙ ሌሎች የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ካሉ በቁጥጥር አደን ቀበሌውና በጥበቃ ቦታዎቹ መካከል 8 (ስምንት) ኪ. ሜትር ደጀን ወይም ነፃ መሬት መኖር አለበት፡፡
13. የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች የስምምነት ውል በየስድስት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
14. ክልሎች የዱር እንስሳት አጠቃቀምን ዘላቂ ለማድረግ እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ከዱር እንስሳት አደን የሚገኘውን ገቢ ለህብረተሰቡ (ለአደን ቀበሌው አካባቢ) ልማት የሚውልበትን ሥርዓት እንዲዘረጉ ባለሥልጣኑ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

15. የአደን ተቆጣጣሪዎች የአደን ቀበሌውን ካርታ በማንበብ አደኑ በአደን ቀበሌው ወሰን ውስጥ መከናወኑን ማረጋገጥና ታዳኙ የዱር እንስሳ የታደነበትን ቦታ ጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔትስ በመመዝገብ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡
16. አሳዳኝ ድርጅቶች ከያዟቸው የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ወሰን ውጭ የታዳኝ ዱር እንስሳት አደንን ማከናውን የለባቸውም፤ ይህን ተላልፎ የተገኘ የአሳዳኝ ድርጅት የባለሙያ አሳዳኝነት ፍቃዱ ለሁለት ዓመት ይሰረዛል፡፡
17. በቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ አንድ ታዳኝ እንስሳ ለአዳኝ ቱሪስት ተሸጦ አዳኝ ቱሪስቱ አደን ቀበሌው ድረስ በመሄድ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ተንቀሳቅሶ አስፈላጊውን አሰሳ ካደረገ በኋላ እንስሳውን ሳያድን ቢመለስ የዱር እንስሳውን በድጋሚ መሸጥ ይቻላል፡፡
18. የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ዘለቄታዊ አጠቃቀም ሥርዓት ለመዘርጋትና የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማጐልበት እያንዳንዱ አሳዳኝ ድርጅት የሕብረተሰቡን የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት አስመልክቶ ያዘጋጀውን ዓመታዊ መርሐ ግብር መሠረት በማድረግ በየሩብ ዓመቱ የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
19. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 18 መሠረት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የአፈፃፀም ሪፖርቱን የማያቀርብ አሳዳኝ ድርጅት ከሕብረተሰቡ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ፡-

    ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣
    ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ፈቃዱ ለስድስት ወር ይታገዳል፣
    ሐ. በሦስተኛ ጊዜ ፈቃዱ ይሰረዛል፣

20. የዱር እንስሳት አጠቃቀም ባለድርሻዎች በተናጠልም ሆነ በመቀናጀት የአደን ኢንዱስትሪውን ለማጎልበት የማስተዋወቅ ሥርዓት ይዘረጋሉ፤ ይህን በሚመለከት በየዓመቱ የሥራ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡

## 6. <u>ጡት አጥቢ የዱር እንስሳት አደን የሚካሄድባቸው ወቅቶች</u>

1. የዱር እንስሳቱን ሥርዓተ-ተዋልዶ ከግምት ውስጥ በማስገባትና የሚወልዱትን እንስቶች ከመረበሽ ለመከላከል ሲባል የጡት አጥቢ የዱር እንስሳት አደን የሚካሄድበት ወቅት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በኦሞ ሸለቆ የሚካሄድ አደን ከሐምሌ እስከ ሰኔ፤

ለ) በጋምቤላና ምዕራብ ወለጋ አካባቢዎች የሚካሄድ አደን ከታህሣሥ እስከ ግንቦት፤

ሐ) በአርሲ፣ በባሌና በሐረርጌ ከፍታማ ቦታዎች የሚካሄድ አደን ከጥቅምት እስከ ሰኔ፤

መ) በአፋርና ኢትዮጵያ-ሱማሌ ክልሎች የሚካሄድ አደን ከጥቅምት እስከ ሰኔ፤

## 7. አደን ስለማገድ

1. በማንኛውም የማደኛ ሥፍራ የዱር እንስሳት ሀብቱ ለአልቂት አደጋ መጋለጡን ባለሥልጣኑ እና በሚመለከታቸው የክልል አካላት በሚያደርጉት የጋራ ጥናት ሲያረጋግጡ በማንኛውም ወቅት አደን እንዳይካሄድ ሊታገድ ይችላል፡፡
2. አሳዳኝ ድርጅቱ የገባቸውን ስምምነቶችና እና ከዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የወጡ እና ወደፊት የሚወጡ ማናቸውንም ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተላልፎ በሀብቱ ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ ሲገኝ እንዳያሳድን ይታገዳል፡፡

## 8. ስለስፖርታዊ አደን የቆይታ ጊዜ እና አፈፃፀም

በቱሪስት አዳኞች ባላቸው ተፈላጊነት መሠረት:-

1. አንበሳ፣ ነብር፣ ጎሽ፣ የደጋ አጋዘን፣ ጉማሬ፣ ሳላ፣ ሰመሪንግ የሜዳ ፍየል፣ አምባራይሌ እና ነጭ ጆሮ ቆርኬ ምድብ አንድ ታዳኝ የዱር እንስሳት ተብለው ተሰይመዋል፡፡
2. በደንቡ ሠንጠረዥ 4 የተጠቀሱ ሆኖም ግን በተራ ቁጥር 3 (ሦስት) ከተጠቀሱት ውጪ ያሉ ምድብ ሁለት ታዳኝ የዱር እንስሳት ተብለው ተሰይመዋል፡፡
3. በደንቡ ሠንጠረዥ 5 የተዘረዘሩት ጅብ (ጠቃጠቆ)፣ ጦጣ (ግሪቬት ወይም ቬርቬት) ፣ ዝንጀሮ (ተራ)፣ ከርከሮ፣ ጥንቸል(ተራ)፣ ኢንሹ (የጉንተርስ)እና ጃርት ምድብ ሶስት ታዳኝ የዱር እንስሳት ተብለው ተሰይመዋል፡፡
4. ታዳኝ የዱር እንስሳቱን በአግባቡ ለማደን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 በተገለጸው መሠረት የአደን ፈቃድ የተሰጣቸው ቱሪስቶች የአደን ላይ ጥቅል የቆይታ ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. ከምድብ አንድ፣ ሁለት የዱር እንስሳ ዝርያ ብቻ ለማደን 26 (ሀያ ስድስት) ቀናት፤

ለ. ከምድብ አንድ፣ ሁለት የዱር እንስሳ ዝርያና ከምድብ ሁለት ሌላ የዱር እንስሳ ለማደን 26 (ሀያ ስድስት) ቀናት፤

ሐ. ከምድብ አንድ፣ አንድ የዱር እንስሳ ዝርያና ከምድብ ሁለት ሌላ የዱር እንስሳ ዝርያ ለማደን 21 (ሀያ አንድ) ቀናት፤

መ. ከምድብ አንድ፣ አንድ የዱር እንስሳ ዝርያ ብቻ ለማደን 15 (አስራ አምስት) ቀናት፤

ሠ. ከምድብ አንድ፣ አንድ የዱር እንስሳ ዝርያና ከምድብ ሶስት ሌላ የዱር እንስሳ ለማደን 15 (አስራ አምስት) ቀናት፤

ረ. ከምድብ ሁለት እና ከምድብ ሶስት የዱር እንስሳ ዝርያ አንድ ላይ ለማደን 15 ቀናት፤

ሰ. ከምድብ ሁለት የዱር እንስሳ ዝርያ ብቻ ለማደን 15 ቀናት፤

ሸ. ከምድብ ሶስት የዱር እንስሳ ዝርያ ብቻ ለማደን 15 ቀናት፤

5. በምድብ አንድ የተጠቀሱትን የዱር እንስሳት በረዳት ባለሙያ አሳዳኝ ማደን የተከለከለ ነው፡፡

6. የመንግሥትን ህጋዊ ፈቃድ ሳይዝ በአሳዳኝነት የሚንቀሳቀስ ባለሙያ አሳዳኝ ወይም ረዳት ባለሙያ አሳዳኝ በአሳዳኝነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ የባለሙያነት ፈቃዱ ይሰረዛል፤ ይዞት የተንቀሳቀሰው ድርጅት ፈቃድ ለአንድ ዓመት ይታገዳል፡፡

7. አሳዳኝ ድርጅት ወይም የድርጅቱ ሠራተኛ በማሳደኛ ቦታው ለልዩ ልዩ የድርጅቱ ሥራ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሞቶ ያገኘውን የዱር እንስሳ ውጤት ለባለሥልጣኑ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

8. በአደን ወቅት ወደ ማደኛ ቦታ መንቀሳቀስ የሚገባቸው የአሳዳኝ ድርጅት አባላት ከድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ ውጪ ባለሙያ አሳዳኝ፣ ሾፌር፣ ቆዳ ገፋፊ፣ አብሳይና የአብሳይ ረዳት እንደ አስፈላጊነቱ ሀኪምና መካኒክ ብቻ ናቸው፡፡

9. ማንኛውም አሳዳኝ ድርጅት የመንገድ መሪና ሌሎች ሠራተኞችን እንደ አስፈላጊነቱ ከአካባቢው ሕብረተሰብ መቅጠር አለበት፡፡

10. ያልተፈቀደለትን ሰው በአደን ቦታ ይዞ በተጓዘ አሳዳኝ ድርጅት ላይ ደንብ እንደተላለፈ ተቆጥሮ የአሳዳኝ ድርጅቱ ፈቃድ ለስድስት ወር ይታገዳል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ማርጣ አለካክ

### 9. ስለዱር እንስሳት ማርጣ

1. ቱሪስት አዳኞች የዱር እንስሳትን በሚያድኑበት ወቅት በዕድሜ ትናንሽ የሆኑ የዱር እንስሳት እና እንስቶች እንዳይታደኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚመደቡት የባለሥልጣኑና የክልል ተቆጣጣሪዎች የታደኑ የዱር እንስሳትን ውጤት /ማርጣ/ በመለካት ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

### 10. ማርጣው የሚለካበት ጊዜ

1. የታደነው የዱር እንስሳ ውጤት አደኑ ከተካሄደ በኋላ ወዲያውኑ በቦታው ላይ ከባለሥልጣኑና ከሚመለከተው ክልል በተወከሉ የአደን ተቆጣጣሪዎች መለካት አለበት፡፡
2. ከአደን መልስ ከሦስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የልኬቱ ውጤት ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

### 11. የዱር እንስሳት ማርጣ አለካክ ዘዴዎችና የማርጣ መጠን

1. የዱር እንስሳው የአደን ውጤት ማርጣው የሚለካው ከብረት በተሠራ ሜትር በመጠቀም በኢንች መሆን አለበት፡፡
2. የዱር እንስሳት አደን ውጤት ማርጣ የሚለካው በዚህ መመሪያ አባሪ 1 ከተራ ቁጥር 1-8 የተዘረዘሩትን ዘዴዎች በመጠቀም ይሆናል፤
3. በሀገራችን የሚገኙ ታዳኝ የዱር እንስሳት ዝቅተኛው የማርጣ መጠን በአባሪ 2 ላይ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡ በአደን ወቅት የሚገኝ ማንኛውም ውጤት ከደረት በላይና የሙሉ ማርጣ ብሎ በመለየት ሪፖርቱ መቅረብ አለበት፡፡
4. የደረት በላይ የዱር እንስሳት ውጤት የራስ ቆዳ፣ የራስ አጥንትና ቀንድን ያጠቃለለ መሆን አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተቀመጠው መሠረት ወደ ውጪ ለመላክ የሚፈፀመው ክፍያ ለእያንዳንዱ የማርጣ ዓይነት የተቀመጠውን ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል፤ ሙሉ ማርጣ በአደን ወቅት የሚገኝ ማንኛውም የዱር እንስሳት ውጤት ስለሆነ ውጤቱን ወደ ውጪ ለመላክ የሚፈፀመው ክፍያ ለሙሉ ውጤት የተቀመጠው ነው፡፡
6. የደረት በላይ የዱር እንስሳት ውጤት ለከርከሮ፣ ለዱር አሣማ ሁለቱም ዝርያዎች እና የጉማሬ ጥርስንም የሚጨምር ይሆናል፡፡
7. የማርጣው ልኬት በዚህ መመሪያ አባሪ 2 ላይ ከቀረበው ዝቅተኛ የማርጣ መጠን በታች ከሆነ በደንቡ ላይ የተቀመጡት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 12. <u>እንስት እና ከተፈቀደው የማርጣ ልክ በታች የሆነ ተባዕት እንስሳ ማደን</u>

1. በደንቡ አንቀጽ 15 (2) በተደነገገው መሠረት፣ የአደን ፈቃድ የያዘ አዳኝ፣

   ሀ) ከተወሰነው የማርጣ መጠን በታች የሆነ የዱር እንስሳ አድኖ ከተገኘ የእንስሳውን የነፍስ ወከፍ ዋጋ በእጥፍ ይከፍላል፡፡

   ለ) እንስት የዱር እንስሳ አድኖ ከተገኘ የወንዱን የነፍስ ወከፍ ዋጋ እጥፍ ይከፍላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ለ) ላይ የተገለጹት የቅጣት ክፍያዎች ገቢ የሚሆኑት ለባለሥልጣኑ ነው፡፡
3. ባለሙያ አሳዳኝ ወይም ረዳት ባለሙያ አሳዳኝ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንስት፣ ከማርጣ ልክ በታች የሆነ ተባዕት እንስሳ ካሳደነ ወይም የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሕግና ደንብ ጥሶ ከተገኘ ወይም ሁለትና ከዚያም በላይ ተመሳሳይ ጥፋቶችን በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ፈጽሞ ከተገኘ ፈቃዱ ለአንድ ዓመት ይታገዳል፡፡

# ክፍል አራት

## ስለአደን ፈቃድ አሰጣጥና መስፈርቶች

### 13. የዱር እንስሳት አሣዳኝ ድርጅት ፈቃድ መስፈርቶች

ከአዕዋፍ በስተቀር ሌሎች የዱር እንስሳትን ለማሳደን የአሣዳኝ ድርጅት ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

1. በሀገር ውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ የተረጋገጠ እንደ እንስሳቱ ዓይነት ለአደን የተፈቀደ የጦር መሣሪያ፤
2. የሙሉ ባለሙያ አሳዳኝነት ፈቃድ ያለው ወይም /መሉ ባለሙያ/ አሳዳኝ በቋሚነት ስለመቅጠሩ የሚገልጽ የስምምነት ውል፤
3. ስምንት ባለሁለት ሰው (3 ሜትር በ2 ሜትር ያላነሰ ስፋት ያላቸው) እና ሁለት ለማብሰያና ለዕቃ መጋዘንነት ሊያገለግሉ የሚችሉ (4 ሜትር በ 4 ሜትር ያላነሰ ስፋት ያላቸው) በድምሩ አሥር ደረጃቸውን የጠበቁ ድንኳኖች፤
4. አንድ የዕቃ ማጓጓዣ ፒክአፕ ፎር ዊል ድራይቭና የመገናኛ ሬዲዮ የተገጠመላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ሁለት ፎር ዊል ድራይቭ ስቴሽን ዋገን የመስክ ተሽከርካሪዎች፤
5. የቱሪስት አደን ሥራውን የሚያከናውንበት የቁጥጥር አደን ቀበሌ በኮንሴሽን ስለመያዙ ሕጋዊ የስምምነት ውልና የኮንሴሽን ክፍያ የፈጸመበት ማስረጃ፤
6. በኮንሴሽን በያዘው የቁጥጥር አደን ቀበሌ ቁጥር ከቤዝ ካምፕ ጋር የሚያገናኝ መገናኛ ሬዲዮና አምስት የአጭር ርቀት መገናኛ ሬዲዮኖች፤
7. ሦስት ክፍል የግል ቢሮ ያለው ወይም ተመሳሳዩን ለአንድ ዓመት መከራየቱን የሚገልጽ ውል፤
8. ከሙያው ጋር አግባብነት ያላቸው ሁለት ምግብ አብሳዮች፣ አንድ የካምፕ ኃላፊ፣ ሁለት የካምፕ ጽዳት ሠራተኞች፣ ሶስት ሾፌሮችና በየአስር ካሬ ኪሎ ሜትሩ አንድ የዱር እንስሳ ጠባቂ /ሬንጀር/፤
9. ብር 1,500, 000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) መነሻ የጥሬ ገንዘብ ካፒታል፤
10. ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ ለመክፈል መስማማቱን የሚገልጽ ውል፤

## 14. <u>የአዕዋፍ አሳዳኝ ድርጅት ፈቃድ መስፈርቶች</u>

አዕዋፍን ለማሳደን የአሣዳኝ ድርጅት ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. ለአእዋፍ አደን የሚያገለግል ጦር መሣሪያ በአዳኝ ቱሪስት ወይም በራሱ ድርጅት አማካኝነት ማቅረብ የሚችል፤
2. በአደን ወቅት የወፎቹን ዓይነትና ስርጭት ለይቶ የሚያውቅ ባለሙያ መጠቀም የሚችል፤
3. አራት ባለ ሁለት ሰው እና አንድ ለማብሰያ ሊያገለግሉ የሚችሉ በድምሩ አምስት ደረጃቸውን የጠበቁ ድንኳኖች ያሉት፤
4. ሁለት ዋስትና የተገባላቸው ፎር ዊል ድራይቭ ተሽከርካሪዎች ያሉት፤
5. ሁለት ክፍል ቢሮና አንድ ክፍል ለአደን ውጤቶች በመጋዘንነት ሊያገለግል የሚችል በድምሩ ሁለት ክፍሎች ያሉት፣
6. ለሥራ ዋስትና ብር 50,000.00 (አምሣ ሺህ ብር) መነሻ የጥሬ ገንዘብ ካፒታል ያለው፣
7. ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ የሚመለከተው የመንግሥት አካል በሚያሻሽለው የዋጋ ተመን መሠረት መክፈል የሚችል ወይም ለመክፈል ውል የገባ፣

## 15. <u>በንስር አሞራ (ፋልከን) የማሳደን ፈቃድ መስፈርቶች</u>

በንስር አሞራ ለማሳደን የአሣዳኝ ድርጅት ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. አሳዳኝ ድርጅቱ ወይም ባለሙያው የአደን ጥያቄውን በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ሞልቶ ማቅረብ፤
2. ለአደን የሚጠቀምበትን ንስር ሙሉ ጤንነት የሚያረጋግጥ የጤና ሠርተፊኬት ማቅረብ፤
3. ንስሩን ይዘው ወደ ሀገር ውስጥ የሚመጡ ቱሪስቶች ከመምጣታቸው በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤
4. ንስሩን በሕጋዊ መንገድ ማስገባትና ይዞ መውጣት፤
5. የአሳዳኝ ድርጅቱንና የቱሪስቱን ውል ማቅረብ፤

6. ለእያንዳንዱ አዳኝ ንስር የማስገቢያ የነፍስ ወከፍ ዋጋ ክፍያና የአሳዳኝ ድርጅቱን ወይም የባለሙያውን ክፍያ በውጭ ምንዛሬ መክፈሉን የሚያሳይ የባንክ ደረሰኝ ማቅረብ፤
7. የቱሪስት አደን ሥራ የሚያከናወንበት የቁጥጥር አደን ቀበሌ በኮንሴሽን ስለመያዙ ሕጋዊ የስምምነት ውልና የኮንሴሽን ክፍያ የፈጸመበት ማስረጃ ማቅረብ፡፡

16. <u>የቱሪስት አደንና የማሳደን ፈቃድ</u>

1. አሳዳኝ ድርጅቱ የአደን ጥያቄውን በተዘጋጀው ቅፅ ላይ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፣
2. የቱሪስት አደን ጥያቄ ለባለሥልጣኑ መቅረብ የሚችለው አደኑ ከሚከናወንበት ጊዜ ቢያንስ አንድ ወር ሲቀረው ነው፡፡
3. የአደን መሣሪያው ዓይነት በካሊበርና በውግ ቁጥሩ ለዱር እንስሳት እንደዝርያው ዓይነት ለአደን የተፈቀደ መሆኑንና ቢያንስ ከ30 (ሠላሣ) ጥይት ጋር መያዙን መረጋገጥ አለበት፤
4. የአሳዳኝ ድርጅቱ ከቱሪስቱ ጋር የተዋዋለውን የውል ሰነድ ማቅረብ አለበት፤
5. አሳዳኝ ድርጅቱ ቱሪስት አዳኙ ለእያንዳንዱ ታዳኝ የዱር እንስሳት የነፍስ ወከፍ ክፍያና የድርጅቱን ክፍያ በውጭ ምንዛሪ መክፈሉን የሚያሳይ የባንክ ደረሰኝ ማቅረብ አለበት፡፡
6. የአደን ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ ባንኮች በቱሪስት አዳኞች ወይም በወኪሎች የሚላከው የውጪ አገር ገንዘብ የሚላክለትን ድርጅትና የሚላክበትን ዓላማ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡
7. የውጪ ቱሪስት እና የአገር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አዳኞች የአደን መሣሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመያዝና ለመጠቀም የሚያስችል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት የተሰጠ የፅሑፍ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
8. የውጭ ዜጋ የአገር ውስጥ ነዋሪ አዳኞች የታደሰ የመኖሪያ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው፤
9. የአገር ውስጥ አዳኞች ለእያንዳንዱ ታዳኝ የዱር እንስሳት የነፍስ ወከፍ ዋጋ ክፍያ ስለመፈጸማቸው የባንክ ደረሰኝ ማቅረብ አለባቸው፡፡

10.የባለሙያ አሳዳኝነት፣ የረዳት ባለሙያ አሳዳኝነትና የተለማማጅ ባለሙያ አሳዳኝነትን ፈቃዶች ለማግኘት ጥያቄ ለሚያቀርብ ሰው፡-

ሀ) የዱር እንስሳቱን ዝርያና ባህርይ፣ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሕጎችንና ደንቦችን እንዲሁም የአደን ደንቦችን ስለማወቁ የጽሁፍ እና የቃል ፈተና ወስዶ ለባለሙያ አሳዳኝነት ሰማንያ ከመቶ (80%)፣ ለረዳት ባለሙያ አሳዳኝነት ሰባ አምስት ከመቶ (75%) እና ለተለማማጅ ባለሙያ አሳዳኝነት ስልሳ አምስት ከመቶ (65%) ውጤት ማግኘት አለበት፡፡

ለ) የጦር መሣሪያዎች አጠቃቀምና የተኩስ ዒላማ የተግባር ፈተና ወስዶ ለባለሙያ አሳዳኝነት ሰማንያ አምስት ከመቶ (85%) ፣ ለረዳት ባለሙያ አሳዳኝነት ሰማንያ ከመቶ (80%) እና ተለማማጅ ባለሙያ አሳዳኝነት ሰባ ከመቶ (70%) ውጤት ማግኘት አለበት፡፡

ሐ) ለባለሙያ አሳዳኝነት ፈተና የሚቀርብ አመልካች ቢያንስ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ማጠናቀቁን የሚገልጽ የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

መ) ለባለሙያ አሳዳኝነት በተመሳሳይ የዱር እንስሳት ሥራ ቢያንስ የ7 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣ ለረዳት ባለሙያ አሳዳኝነት ቢያንስ የ5 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው እና ተለማማጅ ባለሙያ አሳዳኝነት ቢያንስ የ3 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

## 17. <u>የአዕዋፍ አደን ፈቃድ</u>

1. በደንቡ አንቀፅ 20 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ማንኛውም ለአዕዋፍ አደን ፈቃድ የተሰጠው የሀገር ውስጥ አዳኝ አደኑን ማከናወን የሚችለው በተፈቀደለት ቦታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአራት ቀናት ብቻ ነው፡፡

ለ) የቱሪስት አዕዋፍ አደን ፈቃድ የሚያገለግለው ለ10 (አሥር) ቀናት ብቻ ነው፡፡

ሐ) ማንኛውም ለአዕዋፍ አደን ፈቃድ የተሰጠው አካል ማደን የሚችለው ከተፈቀደለት ዝርያዎች በቀን አምስት ዝርያዎች ከእያንዳንዱ ዝርያ ሁለት አዕዋፍ ብቻ ነው፡፡

2. ከሚመለከተው ክልል ወይም ከባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ በሌለበት የአእዋፍ አደን ማከናወን አይቻልም፡፡

3. የአዕዋፍ አደን ፈቃድ ጥያቄ ከሌሎቹ የዱር እንስሳት አደን ተለይቶ ለብቻው መቅረብ አለበት፡፡
4. በእርጥበት አዘል ቦታዎች ውስጥ ከሊድ በተሰሩ የረሽ ጥይቶች (Lead shot) ማደን የተከለከለ ነው፡፡

## 18. <u>በንሥር አሞራ (ፋልከን) ስለማደን</u>

1. በንስር አሞራ የሚደረግ አደን (ፋልኮነሪ) የአሳዳኝ ድርጅት ፈቃድ ክፍያ በደንቡ ሰንጠረዥ 2 ተራ ቁጥር 1 በተደነገገው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2. በንሥር አሞራ የማሳደን ፈቃድ በባለሥልጣኑ ይሰጣል፡፡
3. በንሥር አሞራ ለማደን የሚጠየቅ ፈቃድ ቱሪስት አዳኙ ከንስር አሞራው ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በፋልከን አሳዳኝ ድርጅቱ፣ በአዳኙ ወይም በወኪሉ በኩል መሆን አለበት፡፡
4. በንስር አሞራ የማደን ፈቃድ በፋልከን አሳዳኝ ድርጅቱ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ በኩል የማመልከቻ ፎርሙን በመሙላት፣ አስፈላጊውን መረጃ በማቅረብ፣ ክፍያ በመፈፀምና ለንሥር አሞራው የጤና ማስረጃ፣ የአደንና የፋልከን መከታተያ መሣሪያዎች ፈቃድና ፎቶግራፍ በማቅረብ መውሰድ አለበት፡፡
5. በፋልከን አሳዳኝ ድርጅቱ ወይም ወኪሉ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበና የታደሰ ዓመታዊ ፈቃድ ያለው እንዲሁም በአደን ወቅት ለሚከሰቱ ማናቸውም ችግሮች ኃላፊነት ለመውሰድ የሚችል ድርጅት/ ወይም ግለሰብ መሆን አለበት፡፡
6. በቱሪስት አዳኙና በወኪሉ (ድርጅት ወይም ግለሰብ) መካከል የሚፈረም የአደን ስምምነት ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡
7. ወኪሉ ለአደን የሚመጡትን ቱሪስቶች ብዛት፣ ለአደን የሚቀጠሙባቸውን መገልገያዎች፣ የንሥር አሞራዎችን ብዛት፣ ሕጋዊ የውጪ ምንዛሪ ማዛወሪያ መንገድና በአደኑ ወቅት በአብሮ ተጓዥነት የሚሳተፉትን እና ሕጋዊ የሆኑ የአገር ውስጥ አስጎብኚ ድርጅቶች የተፈጸመ የስምምነት ውል ለባለሥልጣኑ ማሳወቅና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
8. ለፋልከን አደኑ ወደ ሀገር ውስጥ ባንክ ገቢ የሚደረገው የውጪ ምንዛሪ የአገር ውስጥ መጓጓዣ፣ በአብሮ ተጓዥ/ተመልካች ክፍያ፣ የፋልከን ክፍያና የመሳሰሉትን ማናቸውንም ክፍያዎች ጨምሮ በአደን ቆይታ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን መገልገያዎች ክፍያ የሚሸፍን መሆን አለበት፡፡

9. ወኪሉ ለቱሪስት መጓጓዣ የሚሆን ትራንስፖርት ማቅረብ የማይችል ከሆነ በአገር ውስጥ ከሚገኙና ህጋዊ ከሆኑ የትራንስፖርት አቅራቢ ወይም አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የተደረገ የውል ስምምነት ማቅረብ አለበት፡፡
10. በንስር አሞራ ማደን የሚቻለው የባለሥልጣኑና የክልል ባለሙያዎች ባሉበት ብቻ ነው፡፡

## 19. <u>በንስር አሞራ የሚታደንባቸው ቦታዎች፣ ወቅቶችና የኮታ ጣሪያ</u>

1. የአደን ወቅት እና የታዳኝ አዕዋፋትና እንስሳት ዝርያ ዝርዝር በደንቡ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡
2. አንድ ንስር አሞራው በቀን ማደን የሚችለው ከተፈቀደለት ዝርያዎች ከአምስት ዝርያዎች ሁለት፣ሁለት አዕዋፍ ብቻ ነው፡፡
3. የማደኛ ቦታዎች የአደን ኮታ ጣሪያ በየዓመቱ አደኑ በሚካሄድበት ክልልና በባለሥልጣኑ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 20. <u>በንስር አሞራ አደን ወቅት ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች፡-</u>

1. ያለ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ንሥር አሞራውን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም የትኛውንም የፋልከን ዝርያም ሆነ ማንኛውንም አዳኝ ወፍ ዝርያ ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፡፡
2. ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር በንሥር አሞራ ሲያድን ወይም ንሥር አሞራዎችን ሲያዟዙር የተገኘ በአዋጁና በደንቡ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. የንሥር አሞራው ጤንነት የዓለም አቀፍ መመዘኛን ያሟላ መሆኑን ንሥር አሞራው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በግብርና ሚኒስቴር መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በንሥር አሞራ አደን ወቅት ለሚከሰት የንሥር አሞራ ወይም መገልገያ መሳሪያዎች መጥፋት ኃላፊነት አይወስድም፡፡
5. የቱሪስት አዳኙ ወይም ወኪሉ በአደኑ ፈቃድ ያልተካተተውን ታዳኝ የወፍ ዝርያ አድኖ ከተገኘ በደንቡ ሰንጠረዥ 8 (ለ) የተመለከተውን የአእዋፍ ዋጋ አራት እጥፍ ይከፍላል፡፡

6. የቱሪስት አዳኙ ወይም ወኪሉ ለአደን የተከለከለ የወፍ ወይም ማንኛውም የጡት አጥቢ ዱር አንስሳ ዝርያ አድኖ ከተገኘ በአዋጁና እና በደንቡ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
7. የቱሪስት አደኑ የቆይታ ጊዜ 10 (አስር) ቀናት ነው፡፡ ሆኖም ቱሪስቱ ከ10 ቀናት በላይ ለመቆየት ቢፈልግ የተጨማሪ 10 ቀናት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
8. በንስር አሞራ ማደን የሚቻለው የባለሥልጣኑና የክልል ባለሙያዎች ባሉበት ብቻ ነው፤
9. ንስር አሞራዎች የወፍ ጉንፋን (Avian influenza) ወረርሽኝ ከተከሰተበት አካባቢ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት አይችሉም፡፡
10. የፋልከነሪ አደን ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የአደን ፈቃድ እስካላቸው ድረስ በአገር ውስጥ ነዋሪ ለሆኑና ላልሆኑ በሙሉ ይፈቀዳል፡

# ክፍል አምስት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 21. የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመሆን የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ዳር ድንበሩ በውል የተቀመጠና ውል የተፈጸመበትን የማደኛ ቦታ ለባለሃብቱ የማስረከብ፤
2. የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን የውል ሰነድ ዝግጅት ከአካባቢው ነዋሪ ማህበረሰብ ጥቅም ጋር በማይጋጭ መልኩ በግልፅ የማከናወንና የአካባቢው ሕብረተሰብ እንዲያውቀው የማድረግ፤
3. የቁጥጥር አደን ቀበሌው የአካባቢውን ሕብረተሰብ ድጋፍ እንዲያገኝ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫና የጋራ መድረክ የማዘጋጀት፤
4. በሥራ ላይ ያሉትን የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ኮፒ ለውል ተቀባይ የመስጠትና ግንዛቤ የማስጨበጥ፤
5. ከማደኛ ቦታው ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመሆን አፋጣኝ መፍትሄ የመስጠት፤

6. የቁጥጥር አደን ቀበሌው በሚገኝበት ክልል የሚሰሩ የልማት ሥራዎችና በባለሀብቱ የሚሰሩ የልማት ሥራዎች በውሉ ላይ በግልፅ ተለይተው በማያሻማ ሁኔታ መቀመጣቸውን የማረጋገጥ፤
7. ለአደን ተግባር ለሚንቀሳቀሱ ቱሪስቶች ተቆጣጣሪ የዱር እንስሳት ስካውቶችን የመመደብ፤
8. ባለሀብቱ ለሚፈጽመው ማንኛውም ክፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ የመስጠት፤
9. በሕጋዊ መንገድ የታደነውን የዱር እንስሳ አካል በከፊልም ሆነ በሙሉ ለአዳኙ የመስጠት፤
10. በማናቸውም ጊዜ ባለሙያ በማሰማራት የማደኛ ቦታውን አጠቃላይ ሁኔታ የማጥናትና የመገምገም፤

22. <u>ውልን ስለመሰረዝ</u>

ባለሥልጣኑ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቅድሚያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በማንኛውም ጊዜ የስምምነት ውሉን መሰረዝ ይችላል፡፡

23. <u>የባለሃብቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ባለሃብቱ የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ከአደን ጋር ተያያዥነት ያላቸው በደንቡ ላይ የተገለጹትን ክፍያዎች በወቅቱ የመፈጸም፤
2. የታዳኝ የዱር እንስሳቱን ዋጋ በተመኑ መሠረት የፌዴራሉንና የክልሉን በግልጽ በመለየት የክልሉን ድርሻ በክልሉ የባንክ ሂሣብ ቁጥር እና የባለሥልጣኑን ድርሻ በባለሥልጣኑ የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ የማድረግ፤
3. አንድ አዳኝ ለአደን ሀገር ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ በቀጥታ ለሚያገኘው የሙያ፣ የሎጅስቲክስና የመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ ግልጽነት የሰፈነበት ሥርዓት የመዘርጋት፤
4. ከአዳኞች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ገቢ ተገቢውን የፋይናንስ ሥርዓት ተከትሎ እንዲገባ የማድረግና ህጋዊ ደረሰኝ የማቅረብ፤
5. በአንድ የማደኛ ቦታ በአንድ የአደን ወቅት የተፈቀደለትን ዝርያና ከየዱር እንስሳው ዝርያ አንድ ብቻ መሆኑን አውቆ የመተግበር፤

6. ለማደኛ ቦታው የሚያስፈልጉ መሠረተ-ልማቶችን በተፈለገው ዓይነትና በተሰጠው ጊዜ የመዘርጋት፤
7. በማደኛ ቦታው ለሚገኘው የዱር እንስሳት ሀብት ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ፤
8. አደኑ በአካባቢው ሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጥር አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ፤
9. አደን ከማደኛው ቦታ ክልል ውጪ እንዳይከናወን አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ፤
10. ለአደን የሚውሉትን እንስሳት ምንጭ፣ የማሳደኛ ዘዴ፣ የሚሰጠውን የማሳደን አገልግሎት ደረጃና ጥራቱን ገላጭ ጽሁፎችንና ማስረጃዎች በግልጽ የማሳየት፤
11. ከአደኑ ፍጻሜ በኋላ ፈቃድ ሰጪው አካል ባዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ሞልቶና አረጋግጦ በመፈረምና ማህተም በማድረግ የመመለስ፡
12. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ መያዝ ፣ ዱር እንስሳት የማሳደን አገልግሎት ደረጃና ጥራቱን የመግለጽና ለምርመራ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለሚመለከተው አካል ግልፅ የማድረግ፤
13. ባለፈቃዱ የተሟላ የንግድ ሥራ ስያሜ፣ አድራሻ (ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፣ የቤት ቁጥር)፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ፋክስና ኢ-ሜል ለተገልጋዮች በግልጽ በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ ወይም የመለጠፍ፤
14. ለአዕዋፍ አደን የሚውሉትን አዕዋፋት የሚያድንበት ቦታ ወይም ምንጭ፣ የማሳደኛ ዘዴ፣ የሚሰጠውን የማሳደን አገልግሎት ደረጃና ጥራቱን ገላጭ ማስረጃዎች በግልፅ ማሳየት ወይም የመለጠፍ፣
15. ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትንና ወደፊት የሚወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር፤

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈፀም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 25. ቅሬታ ስለማስተናገድ

1. በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 26. ቅጣት

የዚህን መመሪያ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ወገን በአዋጁና በደንቡ እንዲሁም አግባብነት ባለው የወንጀልና የፍትሐብሄር ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 27. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች

1. የዱር እንስሳት አደን አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 25/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህ መመሪያ በሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 28. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 29. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጥቅምት ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡


**አዲስ አበባ ጥቅምት ቀን 2009 ዓ.ም**

## አባሪ 1:- የማርጣ አለካክ ዘዴዎች

በሥዕሉ ላይ እንደተመለከተው ቀንዱ የሚለካው የረጅሙ ቀንድ ርዝመት ሲሆን የርዝመቱ ልኬት የሚወሰደው ከፊት ለፊት ከቀንዱ ሥር ጀምሮ እስከ ጫፍ ድረስ ነው፡፡

ዘዴ 1

ይህ ዘዴ ቀንዳቸው ጠመዝማዛ ያልሆነ ወይንም ቀጥ ያለ የዱር እንስሳት ቀንድን ለመለካት ያገለግላል ። ቀንዳቸው ቀጥ ካለው የዱር እንስሳት መካከል ሳላ፣ ድፋርሳ፣ ናይል ሌችዌ፣ ነጭ ጆሮ ቆርኬ፣ ቆርኬ /ሌልዌል/፣ ቆርኬ /መጋላው/፣ የሚዳ ፍየል /የስመሪንግ/፣ የሚዳ ፍየል /የግራንት/፣ አንገተ ረጅሚ፣ ሰስ ፣ ፌቆ፣ ኢንሹ/ የሶልት/፣ ኢንሹ ፣ /የጉንተር/ ፣ ሚዳቋ፣ ይገኙበታል ። ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ





ከላይ በሥዕሉ ላይ እንደተመለከተው ቀንዱ የሚለካው የረጅሙ ቀንድ ርዝመት ሲሆን የርዝመቱ ልኬት የሚወሰደው ከፊት ለፊት ከቀንዱ ሥር ጀምሮ እስከ ጫፍ ድረስ ነው ።

ዘዴ 2

ይህ ዘዴ ቀንዳቸው ጠመዝማዛ የሆነ የዱር እንስሳት ቀንድን ለመለካት ያገለግላል ። መሰል ቀንድ ያላቸው የዱር እንስሳት የደጋ አጋዘን ፣ የቆላ አጋዘን ፣ አምባራይሌ፣ ውድንቢ፣ ድኩላ /ተራው/፣ ድኩላ /የምኒሊክ/ድኩላ ናቸው ።

አለካኩም ከቀንዱ ሥር ወይም ግርጌ ጫፍ ጀምሮ ወደ ላይ የቀንዱን ጠርዝ( Ridge) ተከትሎ እስከ ላይኛው ጫፍ ድረስ ያለውን ርዝመት በመለካት ነው ። በዚህን ጊዜ ቀንዱ የሚለካበት ኬብል ወይንም ክር ወጥሮ በመያዝ ክሩ ወይም ኬብሉ ወደ ቀንዱ ጎድጓዳ ክፍል / depression/ እንዳይገባ በመጠንቀቅ መለካት ያስፈልጋል ።
ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ፡፡




2


ዘዴ 3

ይህ ዘዴ የጎሽ ቀንድን ርዝመት ለመለካት ይረዳል ። አለካኩም በእንስሳው ግንባር በኩል የሁለቱን ቀንዶች ርዝመት ከአንዱ ቀንድ ጫፍ ጀምሮ እስከ ሌላው ቀንድ ጫፍ የቀንዶቹን የታችኛው ጠርዝ በመከተል መለካት ነው ። ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ።





ዘዴ 4

ይህ ዘዴ የአውራሪስ ቀንድን ለመለካት ይጠቅማል ። አለካኩም የያንዳንዱን ቀንድ ርዝመት ከፊት ለፊት በኩል ከቀንዱ ጫፍ /ሥር/ ጀምሮ እስከ ላይኛው ጫፍ ድረስ በመለካት ነው ። ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ





ዘዴ 5

ይህ ዘዴ የከርከሮ፣ የዱር አሳማ፣ የትልቁ ዱር አሳማ፣ እና የጉማሬ ጥርስን ለመለካት ይጠቅማል። አለካኩም የያንዳንዱ ጥርስ በረጅሙ ጎን በኩል ከሥር ወይም ከመሠረቱ ጀምሮ እስከ ጫፍ ድረስ ያለውን ርዝመት በመለካት የሚካሄድ ነው ። ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ




ዘዴ 6

ይህ ዘዴ የዝሆን ጥርስን ለመለካት ያገለግላል። የዝሆን ጥርስ ክብደት የሚለካው በፓውንድ ነው ። የዝሆን ጥርስ ክብደት በሚለካበት ጊዜ ንጹህ ጥርስ ብቻ መመዘን ይኖርበታል። የታክሲደርሚ ሥራ ውጤት የሆኑ ለምሳሌ ፕላስተር ወይም ሌሎች ነገሮች አብረው ከጥርሱ ጋር እንዳይመዘኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። የሁለቱ ጥርሶች ክብደት ለየብቻ ተለክቶ ወደሚቀርበው ½ ፓውንድ በማጠጋጋት የክብደቱ ልክ ይቀመጣል። ሥዕሉን ይመልከቱ




ዘዴ 7

ይህ ዘዴ ሥጋ በል የሆኑ የዱር እንስሳትን የራስ ቅል ለመለካት ያገለግላል። አለካኩም በራስ ቅሉ ረጅሙ ክፍል ያለውን ርዝመት ከጫፍ እስከ ጫፍ ድረስ በመለካት የሚካሄድ ነው ።ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ።




ዘዴ 8

ይህ ዘዴ የአዞ ርዝመት ለመለካት ያገለግላል። አለካኩም የሚካሄደው የአዞውን ርዝመት ከጫፍ እስከ ጫፍ በመለካት ነው። ይኸውም ከጭራው ጀምሮ በጀርባው በኩል እስከ አፍንጫው ጫፍ ድረስ ያለውን የርዝመት መጠን በኢንች መለካት ነው ። ሥዕሉን ይመልከቱ



አባሪ 2፡- የኢትዮጵያ ታዳኝ የዱር እንስሳት ዝቅተኛ የማርጣ መጠን

| ተ.ቁ | የዱር እንስሳት ስም | ዝቅተኛ የማርጣ መጠን | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚላከው ውጤት | የአለካክ ዘዴዎች | በሴ.ሜ. | በኢንች |
| 1 | ጎሽ | ቀንድ | 3 | 101.6 | 40.0 |
| 2 | ውድንቢ | ›› ›› | 2 | 74 | 29.1 |
| 3 | የቆላ አጋዘን | ›› ›› | 2 | 98 | 38.6 |
| 4 | የደጋ አጋዘን | ›› ›› | 2 | 75 | 29.50 |
| 5 | አምባራይሌ | ›› ›› | 2 | 63.5 | 25 |
| 6 | ድኩላ | ›› ›› | 2 | 25 | 9.80 |
| 7 | የሚኒሊክ ድኩላ | ›› ›› | 2 | 29 | 10.1 |
| 8 | ሳላ | ›› ›› | 1 | 70 | 27.6 |
| 9 | ድፋርሳ | ›› ›› | 1 | 68 | 25.0 |
| 10 | ናይል ሌችዌ | ›› ›› | 1 | 64 | 25.20 |
| 11 | ነጭ ጆሮ ቆርኬ | ›› ›› | 1 | 48 | 18.90 |
| 12 | ብሆር የሜዳ | ›› ›› | 1 | 13 | 7.6 |
| 13 | ብሆር የተራራ | ›› ›› | 1 | 11 | 4.0 |
| 14 | ቆርኬ /ሌልዌል/ | ›› ›› | 1 | 60 | 18.8 |
| 15 | ቆርኬ /መጋላው/ | ›› ›› | 1 | 52 | 17.2 |
| 16 | ቆርኬ ቶፒ | ›› ›› | 1 | 45 | 17.70 |
| 17 | የሰመሪንግ የሜዳ ፍየል | ›› ›› | 1 | 38 | 13.5 |
| 18 | የግራንት የሜዳ ፍየል | ›› ›› | 1 | 61 | 23.1 |
| 19 | አንገተ ረጅሜ (ገረኑክ) | ›› ›› | 1 | 34 | 12.8 |
| 20 | ሰስ | ›› ›› | 1 | 11 | 3.6 |
| 21 | ፌቆ | ›› ›› | 1 | 13 | 4.2 |
| 22 | ኢንሹ /የሶልት/ | ›› ›› | 1 | 6 | 2.4 |
| 23 | ኢንሹ /የጉንተር/ | ›› ›› | 1 | 8 | 2.6 |
| 24 | ሚዳቋ | ›› ›› | 1 | 11 | 3.5 |

| ተ.ቁ | የዱር እንስሳት ስም | ዝቅተኛ የማርጣ መጠን | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚላከው ውጤት | የአለካከ ዘዴዎች | በሴ.ሜ. | የሚላከው ውጤት |
| 25 | ጉማሬ | ጥርስ | 5 | 50 | 19.7 |
| 26 | ከርከሮ | ›› ›› | 5 | 30 | 9.0 |
| 27 | ትልቁ የዱር አሣማ | ›› ›› | 5 | 14 | 5.5 |
| 28 | የዱር አሣማ | ›› ›› | 5 | 11 | 4.33 |
| 29 | አዞ | የሰውነት ርዝመት | 8 | 9 | 3.5 |
| 30 | አንበሳ | የራስ ቅል ርዝመት | 7 | 23 | 9.0 |
| 31 | ነብር | ›› ›› | 7 | 14 | 5.50 |
| 32 | አነር | ›› ›› | 7 | 6 | 2.4 |
| 33 | ዳልጋ አንበሳ | ›› ›› | 7 | 6 | 2.4 |
| 34 | ጥርስ | ›› ›› | 7 | 7 | 2.8 |
| 35 | ጠቃጠቆ ጅብ | ›› ›› | 7 | 15 | 5.9 |